# ዓባይ



ፀሐይ ዳመናው ቁልጭ-ልጭ
በጋው አልፎ ክረምት ገባ፣
ዳመናው ብልጭ-ልጭ
ነጎድጓዱ  ነጎደ፣
መስከረም እስኪጠባ
ወንዙ  ሄዶ  ገደብ አልባ...
አባይ  ተኸርጎደጎደ!



ዝናቡ ዘንቦ-ዘንቦ
መሬቱን ተረተረው፣
ግድብ የለ ገንዳ፣ ገንቦ
አፈሬን አጥቦ-አጥቦ
ቁልቁሊት አምዘግዝጎ
መሬቱን ሸረሸረው
ግብፅ ወስዶ ሊከምረው
ወሰደው ጠራርጎ...



ማነው ፈረሰኛው
ዘምቶ ከወድያ ማዶ
ከባዕድ ምቀኛው
የሚመልስ ያንን
ያገሬ አፈሩን፣
ባሕር-ዛፉ ማገዶ
አለቀ ነድዶ-ነድዶ!





 አንድ በሉልኝ እንጅ
ወንድም ጋሼስ የለም  ወይ?
ስሞትስ  አያይም  ወይ?
ይህ መቸውም አይበጅ
በግብፁ በጠላቴ
ማቀቀ  አካላቴ፣
ተቀጨ ልጅነቴ...

ገ/ኢ. ጐርፉ።

WWW.EthiopianHCC.org

9852 Stanford Av., Garden Grove, CA. 92841   www.EthiopianHCC.org